# <u>አጫጭር ግጥሞች</u>

መች አቃጠለኝ
ቃርያ በርበሬ!
ምነው አይሰሙኝ
አባ መምሬ!
ልቤን አመመኝ
ተንፈራፍሬ፣
ክፉ ነው አሉኝ
ተዋጊ በሬ…

* * *

በሰላም ሲጓዝ የነበረውን…
\- ምንም ሳይጨንቀው፣
ዘልሎ በድንገት ጕረሮውን…
\- አፍኖ አነቀው!
ያዘና ታድያ ጆሮ-ጆሮውን
\- ጥፊ ወልውሎ ለቀቀው!

* * *

ሌባ ተይዞ ዱላ ይጠየቃል!
ገብስ ማሽላ ታ’ውድማ ይወቃል፣
ባልሠራው ሥራ ማ’ ይጨነቃል፣
ፊ’ተጨማዶ ሎሚ ይጨመቃል!

ዱላ ተይዞ ሌባ አይጠየቅም፣
ይደበድቧል!
ሌባ ተይዞ የዱላ አይጠ-መጐጥ፣
ያጕመጠምጠዋል!

* * *

ቀይ ወጥ ነው ወይ ዶሮ፣
ምንቸት አብሽ፣ ክክ፣
ጨጬ፣ ጭኮ፣ ሽሮ፣
ቅንጨ፣ ፍርክርክ፣
አንጀት አሳርሮ
የሚያብረከርክ!

የሚያልፍ መስሎ
ምንም ሳይገድደው፣
ከሽቅብ ዘልሎ
አንገዳገደው፣
በቡጢ ብሎ
አወላገደው…

* * *

አቶ በ’ልኹ
ቀምሰው ድልኹ
ዋ! ብለው ጮኹ…

* * *

ሽምብራና ዓተር፣
ጓያ፣ ባቄላ፣
ቀምሼ ነበር
ያ’ርግልኝ ጤና…
ሽምብራና ዓተር፣ ጓያ፣ ባቄላ፣
ሆድ ቁርጠቱ’ሳ፣ ለምን ይበላ?

ታርሶም፣ ተሸምቶም
ሽምብራና ዓተር፤
ታምሶም፣ ተቆልቶም፣
ይበላ ነበር!
ከተቆላ ቆሎ፣ ከታመሰም እምስ፣
ይሻለኛል ስጋ ጥሬም ሆነ ጥብስ!

* * *

ዝሆንና አውራሪስ
የተራገጡ ዕለት
ለሙጃ፣ ሣር-ቅጠል
እጅግ እዘኑለት…
ወዮለት! ወዮለት!

ገ/ኢ. ጕርፉ።